**የሰ/መ/ ቁጥር 150572**

**ቀን 30/11/2010 ዓ/ም**

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፊይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች - ወ/ሮ በቀሉ ሞገስ ጠበቃ አበበ አለነ ቀርቧል

ተጠሪ - አቶ ኤልያስ አዩብ ጠበቃ ጌታቸዉ ማንደፍሮ ቀርቧል

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ለዚህ ሰበር መዝገብ ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የቀረበው አመልካች ታህሳስ 9 ቀን 2010 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 193780 ህዳር 1 ቀን 2010 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ እና የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 123305 የካቲት 30 ቀን 2009 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ቅሬታውን በማቅረቡ ነው፡፡ ቅሬታውም አቤት የተባለበትን ውሣኔ፣ አመልካች የሚቃወምባቸውን ምክንያቶች የሚዘረዝርና በሰበር ሰሚው ችሎት በኩል ሊታይልኝ ይገባል የሚለውን ዳኝነት የሚጠይቅ ሲሆን፣ የስር ፍ/ቤት ተጠሪ በሰራተኛነት የቀጠረኝ መሆኑን ማስረጃ አቅርቤ እያለ የቀረበው ማስረጃ ከትክክለኛው አካል መሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ እና ትርጉሙም በተዛባ ሁኔታ የቀረበ ሆኖ እያለ እንደ ማስረጃ ተወስዶ ውሳኔ መሰጠቱ ስህተት በመሆኑ ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡

በስር ፍ/ቤት የነበረው ክርክር የጀመረው ከፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን ከሳሽ የአሁን ተጠሪ ባቀረበው ክስ ተከሳሽ የአሁን አመልካች ስትሆን ከሳሽና ተከሳሽ በ 29/1/2005 ዓ/ም በቤሩት ሊባኖስ አገር ጋብቻ ፈጽመን እስከ ጥር ወር 2006 ዓ/ም ሊባኖስ ሀገር በትዳር ቆይተናል፡፡ ከጥር ወር 2006 ዓ/ም ወዲህ ተከሳሽ ወላጆቼን ልጠይቅ ብላ ወደ ኢትዮጵያ መጥታ ሳትመለስ ቀርታለች፡፡ እንድትመለስ ብጠይቃትም እምቢ ብላ ሚያዝያ 19 ቀን 2006 ዓ/ም አቶ ዓለማየሁ ታደሰ የሚባል ሰው አግብታ በደል ፈጽማብኛለች፡፡ በመሆኑም ጋብቻችን ፈርሶ በጋብቻ ላይ ጋብቻ ስለፈጸመችብኝ ካሳ እንድትከፍለኝ ሲል ጠይቋል፡፡ ተከሳሽም ከከሳሽ ጋር ጋብቻ የለኝም፡፡ ከሳሽ ያቀረበው የጋብቻ ማስረጃ ጋብቻ ስለመኖሩ የማያመለክት በመሆኑ ዋጋ የለውም፡፡ በመሆኑም ክሱ ውድቅ ይሁንልኝ፡፡ የምከፍለውም ካሳ አይኖርም በሚል መልስ ሰጥታለች፡፡ የስር የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 123305 የካቲት 30 ቀን 2009 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ ከሳሽ ያቀረበው የጋብቻ ማስረጃ ጋብቻን የሚገልጽ መሆን አለመሆኑን ቤሩት ሊባኖስ ሀገር በቆንሲላ በኩል ጥያቄ ቀርቦለት በከሳሽና ተከሳሽ መሀከል በ 29/1/2005 ዓ/ም በእስልምና ሀይማኖት ሥረዓት መሰረት የተፈጸመ ጋብቻ

ያለ መሆኑን ተረጋግጧል። በመሆኑም በተሻሻለው የፌደራል የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 ድንጋጌ መሰረት በሀይማኖት ሥርዓት የተደረገ ጋብቻ መሆኑ ተረጋግጧል። በሌላ በኩል ተከሳሽ ከከሳሽ ጋር ጋብቻ እያላት ጋብቻ በመፈጸሟ ካሳ ይከፈለኝ ላለው ተቀባይነት ያለው አይደለም። በከሳሽና ተከሳሽ መሀል ያለው ጋብቻ ፈርሷል ሲል ወስኗል። ተከሳሽ ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታ አቅርባ በመ/ቁጥር 193780 ህዳር 1 ቀን 2010 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ የስር የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ውሳኔን በማጽናት ወስኗል።

የአሁን አመልካችም ይህን ውሳኔ በመቃወም ቀርባለች። መዝገቡም ተመርምሮ በስር ፍ/ቤት በዚህ ጉዳይ አመልካች ከተጠሪ ጋር የተፈጸመ ጋብቻ የለም በማለት የቀረበውም የጋብቻ ማስረጃዎች የተምታቱ እና የተለያየ ናቸው በሚል ያቀረበችውን ክርክር በሥር ፍ/ቤቶች ከግንዛቤ ውስጥ አስገብቶ ግራ ቀኙ የተጋቡበት እርግጠኛ ቀን ተለይቶ ሌሎች ማስረጃዎች ደግሞ ለምን ውድቅ መደረግ እንዳለባቸው ሳይገልጽ ጋብቻ አለ የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ቀርቧል። መልስና የመልስ መልስም ተሰጥቶበታል። ተጠሪ የካቲት 7 ቀን 2010 ዓ/ም በተጻፈ መልስ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ መሰረታው የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት መሆኑን በማንሳት ይጽናልኝ ሲል ተከራክሯል። አመልካችም መጋቢት 3 ቀን 2010 ዓ/ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል።

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል፣ እኛም የቀረበውን አቤቱታ፣ መልስ እና የመልስ መልሱን እንዲሁም የስር ፍርድ ቤት ውሣኔዎችን እና ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል። እንደመረመርነውም በስር ፍ/ቤት ክርክር በአሁን አመልካችና ተጠሪ መሀከል ጋብቻ ስለመኖሩ ቤሩት ሊባኖስ ሀገር በቆንሲላ በኩል ጥያቄ ቀርቦለት በከሳሽና ተከሳሽ መሀከል በ 29/1/2005 ዓ/ም በእስልምና ሀይማኖት ሥረዓት መሰረት የተፈጸመ ጋብቻ ያለ መሆኑን ማስረጃ ቀርቦ የቀረበው ማስረጃ የቀን ስህተት ያለው በመሆኑ ይሄው እንደጣራ ተደርጎ ተረጋገጦ ውሳኔ ተሰጥቷል። አመልካች ያነሳችውን ቅሬታ በተመለከተ የስር ፍርድ ቤት ፍሬ ነገር የማጥራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን የተሰጠው ፍ/ቤቶች በቀረቡት ምስክሮችና ማስረጃዎች አጣርተው መዝነው በአመልካችና ተጠሪ መሀከል ጋብቻ ስለመኖሩ ውሳኔ ሰጥተዋል። በኢ..ፌ.ድ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80/3//ሀ/ እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 እና 22 ድንጋጌዎች እንደ ሚያስገነዝቡት በዚህ ችሎት የሚቀርቡት መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመባቸው የመጨረሻ ውሳኔዎች በተመለከተ ነው። የአመልካች የዳኝነት አቤቱታ ደግሞ መሠረታዊ የህግ ስህተት ጉዳይ ሳይሆን ፍሬ ነገር ማጣራትና ማስረጃ ምዘና ጉዳይ በመሆኑ ማስረጃ የመመዘን ለዚህ ችሎት ስልጣን አይደለም። በመሆኑም የስር ፍ/ቤት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም።

## ውሳኔ

1/ መዝገብ ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የቀረበው አመልካች ታህሳስ 9 ቀን 2010 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 193780 ህዳር 1 ቀን 2010 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ እና የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ

ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 123305 የካቲት 30 ቀን 2009 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል።

1. በዚህ መዝገብ ክርክር ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ።

2. የዚህ ውሳኔ ትክክለኛ ግልባጭ እንዲያውቁት ለስር ፍ/ቤት ይድረሳቸው ብለናል።

3. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ፍ